የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No.14
ADDIS ABABA 8th January, 2015

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፫፻፴/፪ሺ፯ ዓ.ም

የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……………………………ገጽ ፯ሺ፱፻፳፰

**CONTENTS**

Regulation No. 330/2014

National Blood Bank Service Establishment Council of Ministers Regulation ……………………………Page 7928

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፴/፪ሺ፯

## የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፩ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፫/፪ሺ፭ እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና ፴፭ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፴/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ደም" ማለት በሰውነት ውስጥ የሚዘዋወር ፈሳሽ ሆኖ በውስጡ ነጭና ቀይ የደም ሴሎች፣ ፕላትሌቶችን እና ፕላዝማ የያዘ ነው፤

፪/ "ደም ልገሳ" ማለት በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ከሰብዓዊ አገልግሎቶች ውስጥ አንዱ የሆነ የሀይማኖት፣ የፆታ እና የዘር ልዩነት የማያደርግ የአብዛኛውን ኅብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ የሚጠይቅ ደም የመስጠት ሂደት ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 330/2014

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE NATIONAL BLOOD BANK SERVICE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 35 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 (as amended by Proclamation No. 803/2013).

**1. Short Title**

This Regulation may be sited as the "National Blood Bank Service Establishment Council of Ministers Regulation No. 330/2014".

**2. Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "blood" means a fluid which circulates within the human body that contains red and white blood cells, platelets and plasma;

2/ "blood donation" means one of a voluntary humanitarian deed of provision of blood irrespective of gender, race and religious differences which requires participation of the public at large;

፫/ "አገልግሎት" ማለት ንጹህ እና በቂ ደም በመሰብሰብ፣ በማዘጋጀትና በማሰራጨት ላይ የሚሠራ ተቋም ነው፤

፬/ "የደም ህክምና" ማለት ደም እና የደም ተዋጽኦ ህመምተኛው መውሰድ እንዳለበት በሕክምና ባለሙያ ሲረጋገጥ የሚሰጥበት ሂደት ነው፤

፭/ "የደም ተዋፅኦ" ማለት ቀይ እና ነጭ የደም ሴሎች፣ ፕሌትሌቶች እና ፕላዝማ ናቸው፤

፮/ "የደም ተዋጽኦዎችን ማዘጋጀት" ማለት ከተሰበሰበው ደም ላይ ቀይ እና ነጭ የደም ሴሎችን፣ ፕሌትሌቶች እና ፕላዝማ በመለየት በየምድባቸው ማዘጋጀት ነው፤

፯/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ ፵፯ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፰/ "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

፱/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

፫. **መቋቋም**

፩/ የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት (ከዚህ በኋላ "አገልግሎት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የአገልግሎቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የአገልግሎቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ስፍራ ቅርንጫፎች ይኖሩታል፡፡

፭. **የአገልግሎቱ ዓላማ**

የአገልግሎቱ ዓላማ በቂ፣ ደህንነቱ የተረጋገጠ እና በወቅቱ የተዘጋጀ ደምና የደም ተዋጽዖዎችን እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸውን አገልግሎቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ደም የሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንዲያገኙ ማድረግ ይሆናል፡፡

3/ "service" mean an autonomous entity which collects, processes and supplies safe and adequate blood;

4/ "transfusion" means giving of blood or blood products to a patient when the patient's need of blood is ascertained by a health professional;

5/ "blood components" mean red and white blood cells, platelets and plasma;

6/ "blood components preparation" means a process of separating red and white blood cells, platelets and plasma from the collected blood parts into their constituent;

7/ "region" means any state referred to in Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

8/ "Ministry" and "Minister" means the Ministry and Minister of Health, respectively.

9/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. **Establishment**

1/ The National Blood Bank Service (hereafter referred to us the "Service") is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality.

2/ The Service shall be accountable to the Ministry.

4. **Head Office**

The Service shall have its head office in Addis Ababa and branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. **Objectives of the Service**

The objective of the Service shall be to provide adequate, safe and timely prepared blood and blood products and other related services to all persons who need blood transfusion in Ethiopia.

**፮. የአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባራት**

የአገልግሎቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም በመገናኛ ብዙሃን እና በሌሎች ዘዴዎች ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር የበጎ ፍቃድ የደም ለጋሾችን ቁጥር ማበራከት፤

፪/ በትምህርት፣ በጤና፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ፣ በሃይማኖት እና በሌሎች መሰል ተቋማት ጨምሮ በሕብረተሰቡ ውስጥ ለተቋቋሙት እና ወደፊት ለሚቋቋሙት የደም ለጋሾች ክበባት ቴክኒካዊ ድጋፍ ማድረግ፤

፫/ ደምና የደም ተዋጽዖዎች ከበጎ ፈቃድ ለጋሾች መገኘቱን ማረጋገጥ፣ ደምና የደም ተዋጽዖዎች መሰብሰብ፣ አስፈላጊውን የላቦራቶሪ ምርመራ ማድረግ፣ ማዘጋጀት፣ ተገቢ በሆነ መልኩ በማከማቸትና ደህንነቱ ተመርምሮ የተረጋገጠ ደም የደም ተዋጽዖዎች ህክምና ለሚሰጡ ጤና ተቋማት ማሰራጨት፤

፬/ የጤና ተቋማትን የደም አገልግሎት ወይም የደም አጠቃቀም ለማሻሻል ማጠናከር፣ በማንኛውም ጊዜ የደም ክምችት በየጤና ተቋማቱ መኖሩን ማረጋገጥ፣ የሆስፒታል ደም ህክምና ኮሚቴዎች መመስረታቸውንና በአግባቡ መስራታቸውን ማረጋገጥ፤

፭/ ለጤና ተቋማት በቂና ደህንነቱ የተጠበቀ ደምና የደም ተዋጽዖ ማቅረብ፤

፮/ በብሔራዊ ደረጃ የደም ክምችት መኖሩን ማረጋገጥ፣ የክልል የደም ባንኮችን ማስተባበር፣ ትስስር መፍጠር እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤

፯/ እንደ አስፈላጊነቱ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር የተገናኙ ምርምሮችን ማካሄድ፣ የአጭር ጊዜና የሥራ ላይ ስልጠና ለሠራተኞች መስጠት እና የአገልግሎት አሰጣጡን በመስኩ ከሚገኘው ዘመናዊ እውቀትና ቴክኖሎጂ ጋር በማዛመድ ማሳደግ፤

፰/ ደም ለመሰብሰብ፣ ለመለየት፣ ለማዘጋጀት፣ ለማሠራጨት፣ ለማስወገድ እና የደም እና የደም ተዋጽዖን ለክሊኒክ አገልግሎት ለማዋል የሚያስችል የአሰራር መመሪያዎችን ማውጣት፤

**6. Powers and Duties of the Service**

The Service shall have the powers and duties to:

1/ enhance the number of blood donors by creating public awareness through mass media and other different means;

2/ provide technical support for blood donor clubs established and to be established in schools, health facilities, governmental and non-governmental organizations, religious institutions and other similar institutions of the community;

3/ ensure that blood and blood products are collected from voluntary donor, collect, conduct necessary laboratory testing, process and store blood and blood products properly and dispatch the screened safe blood and blood products to health facilities providing blood transfusion;

4/ strengthen health facilities to improve their blood service and utilization of blood; ensure the existence of an adequate stock of blood in health facilities and ensure the establishment and proper functioning of hospital blood transfusion committees;

5/ provide safe and adequate blood and blood products to health facilities;

6/ ensure the availability of sufficient stock of blood at national level and, coordinate, network and technically support regional blood banks;

7/ conduct, as may be necessary, researches related to the service, provide short term and on job trainings for staffs and update the service with the modern knowledge and technology in the field;

8/ issue guidelines for collection, screening, processing, providing, discarding and appropriate clinical usage of blood and blood products;

፱/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

፲/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን፡፡

፯. የአገልግሎቱ አቋም

አገልግሎቱ፦

፩/ በሚኒስትሩ የሚመደብ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፪/ አስፈላጊ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

፰. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የአገልግሎቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከተውን የአገልግሎቱን ሥልጣንና ተግባራትን ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የአገልግሎቱን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የአገልግሎቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለአገልግሎቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች አገልግሎቱን ይወክላል፤

ረ) የአገልግሎቱን የስራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

9/ own property, enter into contract and sue and be sued in its own name;

10/ perform other related activities as may be necessary for the attainment of its objectives.

7. **Organization of the Service**

The Service shall have:

1/ a Director General and, as may be necessary, Deputy Director Directors to be appointed by the Minister, and

2/ the necessary staff.

8. **Powers and Duties of the Director General**

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Service and shall, subject to the general directions of the Ministry, direct and administer the activities of the Service.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of the Article the Director shall:

a/ exercise the powers and duties of the Service specified under Article 6 of this Regulation;

b/ employ and administer employees of the Service in accordance with the federal civil service laws.;

c/ prepare and submit to the Ministry the strategic plan, the annual work plan and budget of the Service, and implement same upon approval by the Government;

d/ effect payments in accordance with the approved budget and work plan of the Service;

e/ represent the Service in its dealings with third parties;

f/ prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Service.

፫/ዋና ዳይሬክተሩ ለአገልግሎቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለአገልግሎቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፱. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ስልጣንና ተግባር</u>**

ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚከተሉ ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

፩/ የአገልግሎቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፣

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡት ሌሎች ስራዎችን ያከናውናሉ፣

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው በውክልና የሚሰጣቸውን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

**፲. <u>በጀት</u>**

የአገልግሎቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

**፲፩. <u>የሂሣብ መዛግብት</u>**

፩/ አገልግሎቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የአገልግሎቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

**፲፪. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

አገልግሎቱ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፫. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Service to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Service.

**9. <u>Powers and Duties of the Deputy Director Generals</u>**

The Deputy Director Generals shall have the following powers and duties:

1/ support the Director General in planning, organizing, leading and coordinating the activities of the Service;

2/ perform other duties specifically assigned to them by the Director General;

3/ perform duties specifically assigned to them through delegation in the absence of the Director General.

**10. <u>Budget</u>**

The budget of the Service shall be allocated by the Government.

**11. <u>Books of Accounts</u>**

1/ The Service shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and other financial documents of the Service shall be audited annually by the auditor General or by an auditor designated by him.

**12. <u>Power to Issue Directive</u>**

The Service may issue directives necessary, in consultation with the Ministry, for the implementation of this Regulation.

**13. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publications in the Federal Negarit Gazzette.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of January, 2015.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

3. The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Service to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Service.

9. Powers and Duties of the Deputy Director Generals

The Deputy Director Generals shall have the following powers and duties:

1/ support the Director General in planning, organizing, leading and coordinating the activities of the Service;

2/ perform other duties specifically assigned to them by the Director General;

3/ perform duties specifically assigned to them through delegation and in the absence of the Director General.

10. Budget

The budget of the Service shall be allocated by the Government.

11. Books of Accounts

1/ The Service shall keep complete and accurate books of accounts.

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

2/ The books of accounts and other financial documents of the Service shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

12. Power to Issue Directives

The Service may issue directives necessary, in consultation with the Ministry, for the implementation of this Regulation.

13. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 8th day of January, 2015.

HAILEMARIAM DESSALEGN

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA